- 4 -

ዕቃውን ባዶ ማድረግ

አንድን ዕቃ ከመሙላትህ በፊት መጀመርያ ባዶ ማድረጉ ግድ ነው። ልብም እንደ ዕቃ ናት። ልክ እንደሌላው ዕቃ ሁሉ በሌላ ነገር ከመሞላቷ በፊት ልብም ውስጧ ባዶ መደረግ አለበት። አንድ ሰው ልቡ በሌላ ነገር የተሞላ ሆኖ ሳለ በአላህ ልሙላው ቢል አይቻለውም። ለርሱ ውዳሴ እና ከንዶሎ ነገራት ሁሉ ጥራት የተገባ ይሁን።

ግና ልብን ባዶ ማድረግ ስንል ፍቅርን መከልከል ማለታችን አይደለም። በአንፃሩ አላህ የሚወደው ዓይነት -እውነተኛ ፍቅር- አለ። እሱም አላህ በሚፈልገው መልኩ ብቻ የሆነው ነው። የውሸት ትስስር የሌለበት ንፁህ ፍቅር። ልብን ባዶ እና ንፁህ የማድረግ ሂደት የመጀመርያው እርከን የምስክርነት/ሸሃዳ ቃል ነው። የምስክርነት ቃል ስንል ወደ እስልምና መግቢያ የሆነው ቃል ነው። -ላ ኢላህ ኢልለላህ- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከር።

የመጀመርያው የእምነት ምስክርነት የሚጀምረው ውስጧ የነበረውን ነገር በመሰረዝና ልብን ባዶ በማድረግ መሆኑን ማስተዋል ይኖርብናል። ይህም ከመጀመርያው የሸሃዳ ክፍል ጋር ይመሳሰላል- ላ ኢላህ "አምላክ የለም"- ከሚለው ጋር። ሁለተኛው ደግሞ ባዶ ያደረጉትን ዕቃ መሙላት ሲሆን ከሸሃደ ቀጣዩ ክፍል -ኢልለልላህ- ከአላህ በስተቀር" የሚለውን ይመስላል። ባዶ አድርጎ መሙላት ማለት ይህ ነው እንግዲህ። እውነተኛው የተውሒድ (በአላህ አንድነት ከማመን) ግንዛቤ ላይ ከመድረሳችንና በአንድ አምላክ የማመንን ፅንሰ ሀሳብ ከመረዳታችን በፊት በርግጥም ከአላህ በስተቀር አምላክ አለመኖሩን አስረግጠን መመስከርና በዚሁ ላይ መፅናት ይኖርብናል። "ኢላህ/ አምላክ" ስንል የሚመለክ ነገር ማለታችን ነው። "አምላክ" ስንል የምንሰግድለት አምላክ ብቻ አለመሆኑን መረዳት ግዴታ ነው። አምላክ ስንል የሕይወታችን ማጠንጠኛ፤ የምንግዛው፣ የምንታዘዘው፣ ከዚያም በላይ የሆነ ለኛ አስፈላጊያችን የሆነ ነገር ጌታ ነው. . .

አምላክ ማለት የምንኖርለት ነገር ነው። ያለሱም መኖር አንችልም።

ስለሆነም የትኛውም ሰው እምነት የለሽም ይሁን ኢ-አማኝም፣ ሙስሊም፣ ክርስቲያን፣ አልያም አይሁድ ይሁን ሌላ የራሱ የሆነ አምላክ አለው። እያንዳንዱ ሰው የሆነ የሚያመልከው ነገር ይኖረዋል። የአብዛኛው ሰው አምልኮ ያለው ግን ከዓለማዊ ጉዳዮች ጥቅም አንፃር ነው። ከፊሉ ገንዘብ ያመልካል፤ አንዳንዱ ክብሩንና ማንነቱን ያመልካል፣ አንዳንዱ ዝናውን ያመልካል፣ አንዳንዱ የራሱን እውቀትና ከህሎት ያመልካል።

አንዳንዶች ሌሎች ሰዎችን ያመልካሉ። እና ሌላም ሌላም። አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ ራሣቸውንና ስሜታቸውን የሚያመልኩ ሰዎች እንዳሉ እንዲህ በማለት ገልጿል፡-

﴿ أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴾

«ዝንባሌውን አምላኩ አድርጎ የያዘውን፣ አሳህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን፣ በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን፣ በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አየህን? ታድያ ከአላህ በኋላ የሚያቀናው ማነው? አትገሰፁምን?» (አል-ጃሢያህ :23)

አሁን ባለንበት ዘመን ከእነዚህ በሀሰት ተመላኪ ከሆኑ ነገራት ጋር ነው ራሳችንን እስተሳስረን ያለነው። እነርሱን ነው የሙጢኝ ብለን ያለነው። አብዝተን የተቆራኘናቸው እነኚህ ነገሮች የወደድናቸው ብቻ አይደሉም። በጥልቁና በከፍተኛ ሁኔታ የምንፈልጋቸው ነገሮችም ጭምር እንጂ። እነኚህን ነገሮች ስናጣ ለከፍተኛ ጉዳት እንዳረጋለን። ከአላህ ውጭ ፍፁም በሆነ መልኩ የምንጣበቅበትና እጅ የምንሠጥለት ነገር ካለ በርግጥም ትስስራችን ሐሠተኛ መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ነብዩላህ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ልጃቸውን መስዋእት እንዲያደርጉ የታዘዙት ለምን እንደሆነ እናውቅ ይሆን!?። ልጃቸውን ከመጠን በላይ ይወዱት ነበር። ስለዚህ እርሳቸውን ከምድራዊ የተሳሳተ ትስስሮሽ ነፃ ለማድረግ ተፈለገ። ተፈትነው ነፃ ከሆኑ በኋላ ያ የወደዱት ነገር (የተሳሳተ ተጣምሮት ስላልነበረበት) ተመለሰላቸው።

ከዚህ ዓለም ጥቅሞች ውስጥ ስናጣው እጅግ የምንጎዳበትና ውስጣችን ለሐዘን የሚጋለጥበት ነገር ካለ ያ ትስስር የተሳሳተ ትስስር ነው የሚሆነው። የውሸት ትስስር ባጣነው ጊዜ ለበሽታ የሚዳርገንና ከአላህ (ሱ.ወ.) ውጭ የሆነ ነገር ሁሉ ነው። ስናስበው ጭምር አብዝቶ የሚያባክነን እና ስለዚያ ነገር ማስብ ማቆሙም የሚከብደን ከሆነ ያ ትስስር የውሸት ነው። በከፍተኛ ሁኔታ የምንደነግጥለት ነገር እንኳ ቢሆን ያ ትስስር የውሸት ነውና ልናቆም ይገባል። ያን ነገር የምናሳድደው ከሱ ተለይቶ መኖሩ በእጅጉ ስለሚጎዳን ነው። የጉዳቱ መጠንም እንደ ትስስሮሹ ደረጃ ይለያያል። ትስስሮሹን የፈጠርነው ከገንዘብ፣ ከስሜታችን፣ ከሌሎች ሰዎች፣ ከሆነ ሀሳብ ጋር፣ ከአካላዊ ስህበት፣ ሱስ ከሚያስይዝ ነገር ጋር፣ ከከብራችንና ሥልጣናችን፣ ከሥራችን፣ ከሥማችን፣ ሌሎች ከሚሠጡን ክብር ጋር፣ ከመልካችን፣ ከአለባበሳችን፣ ለሌሎች ለመታየት ከምናደርገው ሁኔታ ጋር፣ ከደረጃችን፣ ከሥራ ማዕረጋችን፣ ከእርጋታችን፣ ከበልጠታችን፣ ከሚዛናዊ አስተሳሰባችንና ወዘተ ጋር ሊሆን ይችላል። እኚህን ሁሉ የተሳሳቱና ሐሰተኛ የሆኑ ትስስሮሾችን እስካልሰበርን ድረስ ልባችንን ባዶ ማድረግ አይቻለንም። ዕቃውን ባዶ

ማድረግ ካልቻልን ልባችንን በትክክል በአላህ ልንሞላው አንችልም።

የኛ ትግል መሆን ያለበት ከሐሰተኛ ነገሮች ጋር ካደረግነው ትስስሮሽ ራሣችንን ማላቀቅ ነው። ልብን ከነኚህ ነገሮች ባዶ ማድረግ በርግጥ ትልቅ ትግልን የሚጠይቅ ነው። ያም ትግል የተውሒድ መሠረታዊ ፅንስ ሀሳብ ነው። በጥልቀት ከመረመርን አምስቱ የኢስላም መስረቶች ከነኚህ ነገሮች ራስን በማላቀቅ ዙርያ የሚሽከረከሩ መሆናቸውን እንገነዘባለን።

ሸሃዳ (የምስክርነት ቃል)፡-

ምስክርነት - ማለትም ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን መመስከር፤ ከዓለማዊ ትስስሮሽ ሁሉ ራሣችንን አላቀን የምንፈልገውን ነገር ለማሳካት በአንደበታችን የምንሠጠው ቃልኪዳን ነው። የዚህም ምስክርነት ትርጉሙ የምናመልከው፣ ፍፁም በሆነ መልኩ የምናምነው፣ የምንወደው፣ የምንፈራውና ተስፋ የምናደርገው አላህን (ሱ.ወ.) ብቻ እና ብቻ መሆኑን ነው። በዚህም ምስክርነታችን ከፈጠረን ጌታ ውጭ ከሌላ ነገር ትስስሮሽ (ቁርኝት) ነፃ እንወጣለን። ይህ ነው እውነተኛው የተውሒድ መገለጫ።

ሰላት (በቀን ውስጥ አምስት ጊዜ)

በቀን አምስት ጊዜ ራሳችንን ከዱንያዊ ጉዳዮች በመነጠል ትኩረታችንን በፈጣሪያችን እና በተፈጠርንበት ዓላማ ላይ እናደርጋለን። በቀን አምስት ጊዜ ከዓለማዊ ጉዳዮቻችን ራሳችንን አቅበን ፊታችንን ወደ ጌታችን እንመልሳለን። ሶላት በቀን አሊያም በሳምንት ውስጥ አንድ ጊዜ ወይም ደግሞ በቀን ውስጥ አምስቱንም ሶላት በየቀኑ አንድ ጊዜ ይፈፀም ዘንድ መታዘዝ ቻለ ነበር። ግና ይህ አልተደረገም። በቀን ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ተበትነው አምስቴ እንድንፈጽማቸው ነው የታዘዝነው። አንድ ሰው ሶላቶቹን ሁሉ በቀን በአንድ በተወሰነ ጊዜ እንዲፈጽም ቢታዘዝ ከዓለማዊ ትስስሮሽ የመላቀቅ ዕድሉ አነስተኛ ነው የሚሆነው። ስለሆነም ለዚህ ነው በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ውስጥ ሶላት እንድትፈፀም ትዕዛዝ የመጣው። ይህ መደረጉ ከዓለማዊ ጉዳዮች የመላቀቁን ሁኔታ ቀላል ያደርጋል። ካልሆነ ዓለማዊ ትስስሮሽን ከአዕምሮ ውስጥ ማስወጣት ከባድ ነው የሚሆነው።

ፆም

ፆም ራስን ከዱንያዊ ትስስሮሽ የምናላቅቅበት አንዱ መንገድ ነው። ከምግብና ከመጠጥ፣ ከወሲብ፣ከመጥፎ ንግግር ራሣችንን እናላቅቅበታለን። በፆም ራሳችን ከአካላዊ ፍላጎቶች በመከልከል መንፈሳችንን እናጠራለን። በፆም ምክንያት ከሥጋዊ ፍላጎታችን፣ ከሚስቡን ነገሮችና ደስታዎች እንላቀቃለን።

ዘካ (ምፅዋት)

ዘካ ራሳችንን ከገንዘባችን ነፃ የምናወጣበትና ለአላህ ብለን ለሌሎች የምንሰጥበት ሁኔታ ነው። ገንዘባችንን በመስጠት ከርሱ ጋር ትስስርና ቁርኝት እንሰብራለን።

ሐጅ (የአላህን ቤት መጎብኘት)

ሐጅ ከዓለማዊ ትስስሮሽ ራሣችንን ነፃ የምናደርግበት ታላቁና ታላቅ እና ምርጥ መንገድ ነው። ወደ ሐጅ በምናደርገው ጉዞ ሁሉንም ነገር ወደኋላ ትተን እንሄዳለን። ቤተሰባችንን፣ ቤታችንን፣ የሞቀ አልጋችንን፣ ምቾት ያላቸው ዘመናዊ አልባሳችንን እንተዋለን። እነኚህን ሁሉ በመተው የሐጅን ሥርዓት ለመፈፀም ስንል ከተለያየ ዓለም ከተውጣጡ አማኞች ጋር በመሆን ስስና ያልተሰፉ ልብሶችን በመልበስ እፍ ብለን ሌጣ መሬት ላይ እንተኛለን። በሐጅ ውስጥ የክብርና የማንነት መገለጫ የሆኑ ነገሮች ሁሉ የሉም። የዝነኞች እና የተለያዩ ብራንድ ልብሶችና ቁሳቁሶች አይኖሩም። ፍራሻችን መሬት፤ ጣርያችን ሰማይ ሆኖ በገላጣ የሙዝደሊፋ ሜዳ ላይ እንተኛለን።

ጌታችን ከዚህች ዓለም ዓለማዊ ጥቅሞች ተላቀቁ ብሎ አላዘዘንም። ባይሆን እንዴት መላቀቅ እንደምንችል የተለያዩ ግዴታዎችን ደነገገብን። ከአምስቱ የእስልምና ማዕዘናት ጀርባ፤ ሌላው ቀርቶ በምንለብሰው ሒጃብም ሆነ ሽፍን ጫማ፣ በምናሳድገው ፂም ውስጥ ጭምር ሚስጥር አለ። ከዓለማዊ ትስስሮሽ የመላቀቅ ሚስጥር። . . .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል "ኢስላም ባይተዋር (እንግዳ) ሆኖ ተጀመረ፤ እንደተጀመረው ሁሉ ባይተዋር ሆኖ ይመጣል። ባይተዋሮች ምንኛ ታደሉ።" (ሶሒሕ ሙስሊም)

በዚህች ምድር ላይ እንደ "እንግዳ" ሆነን እንኖራለን። በላዩዋ እንኖራለን እንጂ የርሷ ዘላለማዊ አካል አይደለንም። ልባችንን ከዓለማዊ ትስስሮሽ ባዶ ማድረግ የምንችለው ከርሷ በመላቀቅና እሷን በሚጠቅማት እና ሕያው ነገር በመሙላት ነው። ልባችንን ከዓለማዊ ፍላጎት ባዶ ካላደረግን በስተቀር ትክክለኛ ምግቧን ልናገኝላት አንችልም። ትክክለኛ መሙያዋም አምላካችን አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው።